# የሀገር ውስጥ ጨረታ ማስታወቂያ

## ጨረታ ቁጥር ሙሲፋ/34/2017

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ አገልግሎት የሚውል አቅጣጫ ጠቋሚ ታፔላ በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ የንግድ ምዝገባና ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው(የ2016/17 ዓ/ም)፤ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ታክስ ከፋይ ተመዝጋቢ የሆኑ የተጠቀሱትን ኮፒ ሰነድ በመያዝ ተጫራቾች የማይመለስ ብር 100.00 ከቫት በፊት በመክፈል የጨረታ ሰነዱን አዲስ አበባ በቅሎ ቤት አካባቢ ጋራድ ህንፃ ቢሮ ቁጥር 432-3-8 ከሚገኘው የግዥ መምሪያ ቢሮ እየቀረቡ መግዛት ይችላሉ፡፡ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ጠቅላላ ዋጋውን 2% በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ስም በባንክ በተረጋገጠ ቼክ (C.P.O) ወይም በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ባንክ ጋራንቲ ከቴክኒክ ዶክመንቶቹ ጋር በማያያዝ ይህ ጨረታ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ጥር 13 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጥዋቱ 3:30 ሰዓት ድረስ በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ የጨረታ ሰነዳቸውን አዲስ አበባ በሚገኘው በግዥ መምሪያ ቢሮ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ጨረታው በዕለቱ ጥር 13 ቀን 2017 ዓ.ም. ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት በግዥ መምሪያ ቢሮ ይከፈታል፡፡

ፋብሪካው ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡


በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን

ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ

ስልክ 0114420216

ፋክስ 0114420688

አዲስ አበባ